# ወላጆች ሊያቀርቧቸው የሚገቡ አስፈላጊ ጥያቄዎች...

## ስንክልና ላላቸው ልጆቻቸው ት/ቤት ሲፈልጉ

በዲሲ የበርካታ ትምህርት ቤቶች ምርጫ ባለበት ሁኔታ ውስጥ፤ ስንክልና ያላቸው ልጆች ወላጆች የሚያጋጥማቸው ከፍተኛ ችግር፤ የትኛው ትምህርት ቤት ነው ለስንኩል ልጆች ጥሩ ፕሮግራም ያለው ብለው የመምረጥ ሁኔታ ነው። ሁሉም ትምህርት ቤቶች የራሳቸው የሆነ የአካባቢ የትምህርት ተቋም( ኤል-ኢ-ኤ LEA (Local education agency) ስላላቸው፣ ዲ-ሲ-ፒ-ኤስ( DCPS) ደግሞ የተለያዩ ፕሮግራሞች ስላለው፤ ልዩ ትምህርትን (special education )በተመለከተ በመንግስት ትምህርት ቤቶቹ ውስጥ አያሌ የተለያዩ ምርጫዎች ስላሉ፤ ወላጆች፤ ለልጃቸው ት/ቤት ሲመርጡ ግምት ውስጥ ማስገባት ያለባቸው የሚከተሉትን ያጠቃልላሉ፤

- በትምህርት ቤቱ የልዩ ትምህርት( special education) የባለሞያዎች አሰላለፍ እንዴት ነው- የልዩ ትምህርት አስተባባሪዎች፣ ከሌሎች ጋር አብረው የሚማሩበትን ሁኔታ የሚያጠኑ ባለሞያዎች፣ የተማሪዎች አገልግሎቶች ሃላፊዎች አሉን? በክፍል በክፍል በደንብ የተመደቡ ናቸውን? የልዩ ትምህርት አስተዳዳሪ ማነው?
- የትምህርት ቤቱ አመራር ስንክልና ያላቸው ልጆች ከሌሎች ተማሪዎች ጋር ተደባልቀው መማራቸውን ይደግፋልን? ከክፍል ውጪ በሚደረጉ ልዩ ልዩ ፕሮግራሞችና እንቅስቃሴዎች ...ወዘተ እንዲካፈሉ ያበረታታልን?
- የተዛመዱ አገልግሎት-ሰጪዎች በ እንዴት ዓይነት አኳሃን ነው የተመደቡት- ግዜያዊ ሰራተኞች( በኮንትራት የሚሰሩ ) አሏቸውን- እነዚህስ በሳምንት ከ 1-2 ቀናት የሚሰሩ ናቸው ወይስ ሙሉ ግዜ የሚሰሩ ናቸው?
- በትምህርት ቤቱ ውስጥ የንባብ ባለሞያዎች አሉን? እነኚህስ በማስረጃ የተረጋገጠ የንባብ እገዛ ያደረጋሉን? ይህ ከሆነ ደግሞ ሰራተኞቻቸው በየትኛው ዓይነት የእገዛ ትምህርት ነው የሰለጠኑት?

ወላጆች፤ ስለ ትምህርት ቤቱ የራሳቸውን ጥናት ማድረግ ይኖርባቸዋል፤ እንደዛም ሆኖ ግን፤ ከአስተማሪዎችና አስተዳዳሪዎች ጋር ፊት ለፊት በአካል ተገናኝቶ መነጋገር የተሻለ ነው። ትምህርት ቤቱን በአካል ተገኝተው ሲጎበኙ፤ የአመራሩ አካል፤ ልዩ ትምህርት የሚያስፈልጋቸውን ተማሪዎች ከሌሎች ተማሪዎች ደባልቆ ማስተማርን የሚመለከተውን መመርያ እንዴት እንደሚመለከተው በደንብ ማስተዋል፤ የተለያዩ ፍላጎቶችን የሚያሟሉ ነገሮች በትምህርት ቤቱ ውስጥ አሉን፤ ምን ያህል እገዛዎች ናቸው ለተማሪው የሚደረጉለት፤ የአስተማሪዎች ወይም የሰራተኞች የክፍል አሰላልፍስ እንዴት ነው የሚሉ ጉዳዮችን ማስተወል ይገባል።

በቅድሚያ፤ **በተቻለ መጠን ጉዳዩን በትክክል የሚመለከቱ አያሌ ጥያቄዎችን ይጠይቁ።** የትምህርት ቤቱ ሰራተኞች በተለይም በልዩ ትምህርት ውስጥ የሚሰሩ ሰራተኞችን ካነጋገሩ የሚያስፈልጎትን መረጃ ሊያገኙ ይችላሉ ከእነሱም ብዙ ሊያውቁ ይችላሉ።

1. 1ልጅዎ በደንብ የታወቀ ስንክልና ካለበት፤ ለምሳሌ ኦቲዝም (Autism) ካለበት፤ ትምህርት ቤቱ ከአሁን ቀደም ኦቲዝም ያላቸው ተማሪዎች ነበሩትን? ቁጥራቸው ስንት ይሆናል? በአሁኑ ወቅት ኦቲዝም ያላቸው ስንት ተማሪዎች አሉት? ስንተኛ ክፍል ናቸው የሚሉትን ጥያቄዎች ይጠይቁ።
2. የ እንዲህ አይነቶቹን ልጆች ፍላጎት ለማሟላት፤ ትምህርት ቤቱ የመማርያ ክፍሎችን ወይም የትምህርት ዓይነቶችን በእንዴት ዓይነት አኳሃን ነው የሚያቀነባበረው፤ የተለይየ የትምህርት መመርያዎችን ይሰጣልን፤ ለምሳሌ ከአንድ ትምህርት ወደ ሌላ( ከክፍል ወደ እንቅስቃሴ ክፍል(ጂም) መሸጋገርያ ወቅት፤ ትምህርት ቤቱ የሚጠቀምባቸው የጠባይ ማረምያዎች ወይም ማስተካከያዎች አሉትን?
3. ትምህርት ቤቱ የሚከተለው የልዩ ትምህርት ሞዴል( model) ምንድነው? ምናልባት ካስፈለጋቸው ተማሪዎች በአነስተኛ ቁጥር ሊማሩባቸው የሚችሉ የተለዩ ክፍሎች አሉትን ?
4. ትምህርት ቤቱ የጥሩ ጠባይ እገዛ ፕሮግራም አለውን? በዚህ ኢጋዥ ስልት የሰለጠኑ አስተማሪዎች አሉትን? (በየስንት ግዜ ይሰለጥናሉ) ፤የጠባይ ጣልቃ ገብነት ፕሮግራም (Behavior Intervention Plans (BIPs) ከሚባለው ጋርስ እነዚህ የትምህርት ቤቱ ዕቅዶች ምን ያህል ይቀናጃሉ?
5. ከጠባይ ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን እንዴት ነው ት/ቤቱ የሚፈታው? አስተማሪዎች የኤ-ቢ-ኤ (ABA) ስልጠና ያገኛሉን ወይም ስንክልና ያለባቸውን ልጆች በማስተማር በኩል ሊያግዛቸው የሚችል ትምህርት ይሰጣቸዋልን? ትምህርቱን ለማካሄድ የሚረዳቸው ቴክኖሎጂስ ቀርቦላቸዋልን?መልሱ አዎን ከሆነ ምን?
6. ችግር በመፍታት በኩል የሚያግዛቸው የቴክኖሎጂ እርዳታ አላቸውን? ይህ ካላቸው ምን ዓይነት?
7. ከትምህርት ጋር የተዛመዱ አገልግሎቶች (ምክር/የንግግር ትምህርት/ ኦቲ( OT) እንዴት ነው የሚሰጡት? እነኚህን አገልግሎቶች የሚያቀርቡ ተቋሞች (ኦቲ (OT)፣ ኤስ-ኤል-ፒ( (SLP )እና ፒቲ( PT) በትምህርት ቤቱ ውስጥ ምን ያህል ግዜ ነው በአካል የሚገኙት?(ምክር ሰጪው ሓኪም፤ ሄዶ ምክሩን እንዲያበረክት የተመደቡለት የትምህርት ቤቶች ቁጥር ከ 2-4 ሊሆን ስለሚችል፤ ባለሙያው፤ ልጅዎ ባለበት ትምህርት ቤት ውስጥ ምናልባት በሳምንት አንድ ቀን ብቻ ሊመጣ ይችላል። ይህም ልጁ ሊጠቀምበት የሚችለውን ምክር ለምሳሌ ንግግር የማሻሻያ ትምህርት፤ ከአስተማሪዎችና ከምክር ሰጩው ሓኪም ጋር የተቀናጀ ትምህርት ለመስጠት ሊኖር የሚችለውን ትብብር የተወሰነ ያደርገዋል።
8. በትምህርት ቤቱ ውስጥ ምን ያህል ልጆች ናቸው ለግላቸው የተዘጋጀ የትምህርት ፕሮግራም (አይ-ኢ-ፒ IEP) ያላቸው? በየክፍሉ ምን ያህል የተማሪዎች ቁጥር አለ?
9. በትምህርት ቤቱ በሞላ ስንክልና ያላቸው ተማሪዎች ቁጥር ም፣ን ያህል ነው?
10. የአያሌ ስንክልና ቡድኑ (ኤም-ዲ-ቲ MDT (Multiple Disability Team) ወይም ኤስ-ኤስ-ፒ( SSP) የትምህርት እገዛ ቡድን (School Support Team) በየስንት ግዜ ይሰበሰባሉ?
11. ትምህርት ቤቱ ምን ያህል የልዩ ትምህርት አስተማሪዎች አሉት? እነኚህ የልዩ ትምህርት አስተማሪዎች እንዴት ነው በስራቸው የተመደቡት ( በክፍል ነው ወይስ እንደየአስፈላጊነታቸው? የስራ ጭነታቸውስ ምን ያህል ነው?
12. ማነው እንደ ልዩ ትምህርት አስተባባሪ በመሆን በመስራት ላይ የሚገኘው? የተማሪዎቹ ጉዳይ አስፈጻሚ ሆኖ የሚያገለግል ማነው?


**ለፍትህና ትምህርት የቆሙ ጠበቃዎች ድርጅት**

*በመንግስት የረቀቀ ለዋሽንግተን ዲሲ ወላጆች ስልጠናና መረጃ ማእከል*

www.aje-dc.org | (202) 678-8060 | information@aje-dc.org

**ትምህርት ቤቱ የሚከተለውን የትምህርት ሂደት ለመረዳት የሚከትሉትን ጥያቄዎች ይጠይቁ፣**



1. ባሏችሁ ፕሮግራሞች፤ ምን ዓይነት ተማሪዎች ናቸው የበለጠ ይጠቅማሉ ብለው የሚያምኑት? ባሏችሁ ፕሮግራሞች ችግር ያለበት ማንኛውም ተማሪ ሊጠቀም ይችላልን ?
2. በንባብ/በቁጥር/ በአጻጻፍ ከማለፍያው ደረጃ በታች ለሆኑ ልጆች እንዴት ነው እገዛ የምታደርጉላቸው?
3. ልጆች የትምህርት/የማህበራዊ ግንኙነትና የጠባይ ችግር ሲያሳዩ እንዴት ነው ወላጆችን የምታሳውቋቸው?
4. ምን አይነት ተጨማሪ ድጋፎች (ለምሳሌ ከትምህርት ውጪ የሚሰጡ የትምህርት ፕሮግራሞች) ነው የምትሰጡት?
5. ማህበራዊ ችግር ወይም ጓደኛ የማግኘት ወይም ከ እኩያዎቻቸው ጋር ጥሩ ግንኙነት የመፍጠር ችግር ያለባቸውን የምታግዟቸው?
6. ልጄ፤ ትምህርት ከሚጀመርበት ግዜ በፊት፤  ቀደም ብሎ ትምህርት ቤት በመምጣት ከአስተማሪው ጋር በግል ተገናኝቶ ምን እንደሚጠበቅበት ለማወቅ የሚያስችል ዕድል ማግኘት ይችላልን?  በበጋ ወራት የሚሰጥ ፕሮግራም አለን? የዚህ ፕሮግራም ትኩረት በትምህርት ላይ የተመረኮዘ ነው ወይስ አዲስ ትምህርት ቤቱን ለመለማመድ በሚረዱት ነገሮች?
7. እኔ ወይም ልጄ ስለትምህርት ቤቱ ጥያቄ ቢኖረን ከማን ጋር ነው መነጋገር ያለብን?

**በግል የሚዘጋጅ የትምህርት ፕሮግራም (IEP) የተደረገላቸው ተማሪዎች ወላጆች ጋር ለመነጋገር ጠይቁ፡፡ ከአንድ ወላጅ ለሌላ ወላጅ የሚጠየቅ ጥያቄ፤**

*እንደ ወላጅ መጠን፤ ትምህርት ቤት ውስጥ ሲመጡ፤ ምን አይነት "ስሜት ይሰማዎታል"? ማለትም ልዩ ትምህርት ከሚሰጡት የ ቡድን አባላት(የ አይኢፒ IEP) ጋር  አንድ አካል የሆኑ ሆኖ ይሰማዎታልን? ወደ ትምህርት ቤቱ ሲመጡ ጥሩ አቀባበል ይደረግሎታልን? ልዩ ትምህርቱንና የአስተዳደር አባላትን እንዴት ይገልጿቸዋል- ስራቸውን በደንብ እንደሚያውቁ ባለሙያዎች ? ስለጉዳዩ እውቀት እንዳላቸው?እምነት ሊጣልባቸው እንደሚችሉ ?*

ይህ ሁሉ ጥያቄ፤  የልጅዎን ዓይነተኛ ጠባይ ለመጠቃቀስ ና ንግግር ለመጀምር ጥሩ መነሻ ይሆናል እንጂ መጠየቅ የሚገባውን ሁሉ የሚያጠቃልል ዝርዝር የያዘ አይደለም። ለምሳሌ ልጆቹን ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ማሻገር ምን እንደሚመስል እንደ አርእስት ሲነሳ፤ ልጅዎ የድምጽ ብዛትና ጩሀት እንደሚረብሸውና ብዙ ሰው ወደ ተሰበሰበበት የጂምናስቲክ ክፍል ሲገባም ጭራሹን መረን እንዲለቅ እንደሚያደርገው መግለጽ ይችላሉ። እንደ ወላጅ መጠን አያሌ አስፈላጊና ምክንያታዊ የሆኑ ጥያቄዎችን ሲጠይቁ፤ አስተማሪዎችና የትምህርት ቤቱ ሰራተኞች፤ ቢያንስ ቢያንስ ልጅዎ ምን ያህል እገዛና አገልግሎት እንደሚያስፈልገው እንደተረዳ ወላጅ ሊያዮት ይችላሉ። ልጅዎ፤ በዲሲ የመንግስት ትምህርት ቤቶች ውስጥ ትምህርቱን በደንብ ለመከታተል የሚያስችሉትን እርዳታዎች፤ ሊሰጥ የሚችል አገልግሎቶችን ማግኘቱን ማረጋገጥ መብትዎ ነው።  **አስታውሱ፤ ልጅዎን ሊያስገቡት ባሰቡት ትምህርት ቤት ውስጥ፤ አስፈላጊ የሆኑ ጥያቄዎችን መጠየቅና ልጅዎ ምን ዓይነቶች የትምህርት ፍላጎቶቹ መሟላት እንደሚያስፈልገው፤ እንደ ወላጅ መጠን፤ ከትምህርት ቤቱ አስተማሪዎችና የመሪ አካል ጋር መመካከር የእርሶ ሃላፊነት ነው። ልጅዎ አንዴ ወደ ትምህርት ቤቱ ከገባም በኋላ የሚያስፈልገው ሁሉ በቀጣይነት እንዲሟላለት ለልጅዎ ጠበቃ መቆሞን መቀጠል አለቦት።**

አንዴ ትምህርት ቤቱን ከመረጡና ልጅዎን ካስመዘገቡ በኋላ፤ የልጆን ሰኬታማነት ለማረጋገጥ፤ ለሚከተሉት ጉዳዮች ጠበቃ መቆም አለቦት፤

- ⇒ በልጅዎ አዲስ ትምህርት ቤት ውስጥ፤ የልዩ ትምህርት አስተባባሪ ጋር ለመገናኘት የምትችሉበትን መንገድ ጠይቁ፤ ትምህርት ከመጀመሩ በፊት፤ የልጅዎን ለግል የሚዘጋጅ የትምህርት ፕሮግራምን( IEP) ወይም የ504 ዕቅድን ቅጂ ለአስተማሪው ይስጡ።
- ⇒ ልጆን በተመለከተ ያሎትን ተስፋና የሚጠብቁትን መሻሻል ለአስተማሪዎች ይግለጹ፤ ልጅዎ ምን ዓይነት ሰው መሆኑንም ለምሳሌ ድክመቱንና ሃያል ጎኖቹን፣ የሚፈታተኑት ጉዳዮችን፣ የሚያስጨንቁትን ነገሮች፣ የትምህርት ችግሮቹንና ሌላም ሌላም ነገሮችን) ከአስተማሪዎቹ ጋር ተካፈሉ። እንደ ወላጁ መጠን፤ ልጅዎን ከ እርሶ በላይ የሚያውቀው የለም።
- ⇒ ትምህርት ቤት አንዴ ከተጀመረ በኋላ፤ የልጆን የቤት ስራ በደንብ ተከታተሉ። ገና በግዜም፤ ከአስተማሪዎቹና ከትምህርት ቤቱ አስተዳዳሪዎች ጋር በቀጥታ እየተገናኙ ተወያዩ፡፡፡ ትምህርት ቤት በተጀመረበት በበልግ ወቅት በወር አንዴ ስብሰባ እንዲደረግ ጠይቁ።

**ኤ-ጄ-ኢ (AJE) ልዩ ትምህርትን በተመለከተ፤ ለወላጆች ነጻ ስልጠናና ምንጮችን ይሰጣል።**
**በዌብሳያታችን ውስጥ ወደ www.aje-dc.org በመግባት ከኤ-ጄ-ኢ (AJE) ጋር ወቅታዊ ይሁኑ፤**
**ወደ information@aje-dc.org በመጻፍ ደግሞ መደበኛ ኢሜላችንና ጋዜጣችንን ለማግኘት ይፍርሙ**

## መቼ ነው ከ ኤ-ጄ-ኤ( AJE) ጋር መገናኘት ያለቦት?

- የልጅዎን የትምህርት ሁኔታ  በተመለከተ ልጅዎ ስላሉት መብቶች ማወቅ ሲፈልጉ
- የልዩ ትምህርቱን ሂደት በተመለከተ ጥያቄ ወይም የሚያሳስቦት ነገር ሲኖሮት (ለምሳሌ (504 proces)፣ የቋንቋ ትምህርት አገልግሎት፣ የኤስ-ኤስ-ቲ ሂደት (SST process )፤ የመሸጋገርያ ወቅት ወይም የጤና እንክብካቤ)
- ለልጅዎ መጣበቅ እንዲችሉ የሚያስፈልጎትን ስልጠና ማግኘት ሲፈልጉ
- የልጅዎ ትምህርት ቤት አንድ ዓይነት ስንክልና ላለው ልጅዎ የሚያስፈልገውን አገልግሎት ሳይሰጥ ሲቀር
- ልጅዎ በትምህርት ቤት ውስጥ በትምህርትም ይሁን በጠባይ  መጥፎ ስነምግባር ሲያሳይ ወይም የጠባይ ችግር ሲያጋጥመው
- ልጅዎ ወደ ትምህርት ቤት እንዳይመጣ ሲታገድ ወይም ከትምህርት ቤት ሲባረር መቼ  ከሌሎች ወላጆች ስሜታዊ እገዛ ሲያስፈልጎት

**ኤ-ጄ-ኢ (AJE) ሊረዳዎት ዝግጁ ነው !**